# ጋዜጣዊ መግለጫ

**ጥቅምት 09 ቀን 2017 ዓ.ም**

**ዘመን ባንክ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከግብር በፊት 3.77 ቢሊዮን ብር ትርፍ አስመዘገበ**

**የባንኩ ዓመታዊ ትርፍም በ36.8 በመቶ አደገ**

**የአንድ አክሲዮን ትርፍ (Earning Per Share) 37.6 በመቶ ሆኗል**

ዘመን ባንክ በ2016 (እ. አ. አ 2023/24) በጀት ዓመት ከግብር በፊት 3.77 ቢሊዮን ብር ማትረፉንና የአንድ አክሲዮን ትርፍ 37.6 በመቶ መሆኑን በዛሬው ዕለት በሚሌኒየም አዳራሽ በተካሄደው 16ኛ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ተገለጸ።

ባንኩ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት እቅዱን ሙሉ በሙሉ በማሳካት ያገኘው ትርፍ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ1.01 ቢሊየን ብር ወይም በ36.8 በመቶ ብልጫ አለው። ባለፉት አምስት ዓመታት ባንኩ በአማካይ ለአንድ አክሲዮን የከፈለው ትርፍ 44.28 በመቶ ደርሷል።

ዘመን ባንክ በ2016 በጀት ዓመት ቁልፍ በሆኑ የውጤታማነት መለኪያ መስፈርቶች ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል። በዚህም የባንኩን አጠቃላይ ሀብት በ23.9 በመቶ በማሳደግ ወደ 59.2 ቢሊየን ብር አድርሷል። በተጠናቀቀው በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የደንበኞች ተቀማጭ ገንዘብ ከቀደመው ዓመት በ17.6 በመቶ አድጎ 43.61 ቢሊየን ብር ደርሷል። የብድር መጠንም ወደ 35.63 ቢሊየን ብር ያደገ ሲሆን የ13.5 በመቶ ብልጫ አለው።

በዚህ ዓመት የባንኩ የውጭ ምንዛሬ ግኝት 566 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር የደረሰ ሲሆን ይህም በየወሩ በአማካይ 47.2 የአሜሪካ ዶላር እንደሆነ ያመለክታል። በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጠናቀቂያ ላይ በመላ አገሪቱ የተቀላጠፈ አገልግሎት የሚሰጡ ቅርንጫፎቻችን ቁጥር 125 ደርሷል።

ባንኩ የካፒታል መሰረቱንና የገንዘብ አቅሙን እያሳደገ የተከፈለ ካፒታሉን 7.5 ቢሊዮን ብር ያደረሰ ሲሆን ይህም ከቀደመው በጀት ዓመት በ2.45 ቢሊዮን ብር ከፍ ያለ ነው። በአሁኑ ወቅት አጠቃላይ የባንኩ የተፈረመ ካፒታል 14.97 ቢሊየን ብር ሆኗል። በበጀት ዓመቱ መጠናቀቂያ ላይ የነበረው የካፒታል ብቃት ጥምርታ (Capital Adequacy Ratio) በተቆጣጣሪ መ/ቤት ከተቀመጠው 8 በመቶ አነስተኛ ጥምርታ ከፍ ብሎ 30.6 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም ውጪያዊ ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች በመቋቋም ጠንካራ የካፒታል አቅም እንደገነባ ያመለክታል።

ወ/ሮ እንዬ ቢምር፣ የዘመን ባንክ አ.ማ የዲሬክተሮች የቦርድ ሰብሳቢ፣ በጉባዔው ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ዘመን ባንክ በ2016 በጀት ዓመት ፈታኝ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በመቋቋም በተለያዩ የሥራ አፈጻጸም መመዘኛዎች አስደናቂ ውጤት እንዳገኘ ገልጸዋል።

አቶ ደረጀ ዘበነ፣ የዘመን ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ በበኩላቸው "ባንካችን ባለአክስዮኖችንና ደንበኞችን የበለጠ ተጠቃሚ ለማድረግ ያለው ቁርጠኛነት አሁንም የጸና ነው። ቅርንጫፎቻችንን የማስፋት፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተልማታችንን የማሳደግ፣ የዲጂታል አቅማችንን የማጎልበትና የምንሰጣቸውን የአገልግሎት አይነቶች የማስፋት ጥረታችንን ቀጥለናል። ሊከሰት የሚችልን አደጋ ለመከላከል ያደረግነው ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድና የባንክ አገልግሎት ብቃታችንን ማሳደጋችን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በስኬት እንድናልፍ አስችሎናል።" በማለት ገልጸዋል።

አቶ ደረጀ የባንኩን የወደፊት አቅጣጫ አስመልክቶም በገበያ ውስጥ ያለውን ተወዳዳሪነት ለማጎልበት፣ ስትራቴጂውን ከወቅታዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ጋር ይበልጥ ለማዛመድ፣ በአካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ ጉዳዮችና መልካም አስተዳደር (ESG) ላይ የበለጠ በማተኮር እንዲሁም እያደገ ከመጣው የቁጥጥርና ክትትል ማዕቀፍ አንጻር ራሱን ብቁ አድርጎ ለመቀጠል ጠንክሮ እንደሚሠራ አስታውቀዋል። ከዚህ በተጨማሪ ዘመን ባንክ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ለማብዛትና ለማሳደግ፣ እንዲሁም ለደንበኞቹ ልዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ሀብት የማሰባሰብ ስራውን ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ ገልጸዋል። የሀገራችንን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶችን ለመደገፍም ከአነስተኛ ንግድ እስከ ኮርፖሬት ኩባንያዎች በልካቸው እንደመልካቸው በልዩነት ያገለግላል ብለዋል።

ዘመን ባንክ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የተለያዩ ስልታዊ የአጋርነት ስምምነቶችን በመፈፀም ተቋማዊ አቅሙን አጎልብቷል። ከእነዚህም መካከል ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን (IFC)፤ ከኢትዮጵያ የሰነዶች ሙዓለንዋይ ድርጅት (ESX)፣ ከሳፋሪኮም ኤም-ፔሳና ከተለያዩ የፋይናንሻል ቴክኖሎጂ አቅራቢዎች ጋር በአጋርነት መሥራት ጀምሯል።

ባንኩ ማህበራዊ ሐላፊነቱን ከመወጣት አንፃርም ለማህበረሰብ ልማት አስተዋጽኦ በሚያደርጉ የትምህርት ቤት የምገባ ፕሮግራም፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ ለአቅመ ደካማ ዜጎች በሚሰጥ ድጋፍና በመንግስት አስተባባሪነት በሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል።

## ስለ ዘመን ባንክ ዳራ

ዘመን ባንክ በ2001 ዓ.ም የተመሰረተ ሲሆን ዓላማውም በሀገራችን በተለየና ዘመናዊ በሆነ አሠራር አዳዲስና የተመረጡ የባንክ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ላይ ያተኮረ ነው። ተቋማዊ ተልዕኮውም ልዩ የሆነ የፋይናንስ አቅርቦት፣ ምቹ የሥራ ከባቢን መፍጠር፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ዘላቂ ጥቅምን ለሁሉም ባለድርሻ አካላት መስጠት እንዲሁም ማህበራዊ ሐላፊነትን በአግባቡ መወጣት ላይ ያተኩራል። ራዕይውም፤ ልዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ማቅረብና የላቀ የአገልግሎት ማዕከል መሆን ነው።

ዘመን ባንክ በጠንካራ የፋይናንስ እንቅስቃሴ፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና በላቀ የደንበኞች አገልግሎቱ ይታወቃል። ባለፉት 16 ዓመታት የሥራ አድማሱን በማስፋትና በአንድ ቅርንጫፍ ከሚሰጥ ኮርፖሬት አገልግሎት በመነሳት ቅርንጫፎቹን በማብዛት ለሁሉም ደንበኞቹ ይበልጥ ተደራሽ ሆኗል። በተጨማሪም አዳዲስና ስኬታማ አሠራሮች በማቅረብ ለሀገራችን የምጣኔ ሀብት እድገትና ለባንክ ዘርፍ ምህዳር ተጠቃሽ የሆነ አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው።

**ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፤**

**ዘመን ባንክ አ.ማ**

**ማርኬቲንግና ኮርፖሬት ኮምዩኒኬሽንስ መምሪያ**

**+251-116 68 68 76**

**www.zemenbank.com**